# ስለ ቤት ምዝገባ ይመለከታል!

በግል ተመዝገበውም ሆነ በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ተደራጅተው በኢትዮጵያ ቤት ለመገንባት ፍላጐት ያላቸው በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

**ለኢትዮጵያውያን**

- ✓ የፀና ፓስፖርት ቅጂ
- ✓ የሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አደረጃጀች ባሉባቸው አገሮች የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ወይም በሚሲዮኑ ተረጋግጦ የሚሰጥ ማስረጃ፣
- ✓ ያገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
- ✓ ያላገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን
- ✓ ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ
- ✓ ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
- ✓ ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትደር ጓደኛ ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤት ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
- ✓ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ በዩሮ ፣ በፓውንድ) የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚዮስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመወሰድ ዝግጁ የሚሆን፣
- ✓ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ፣

**ለትውልደ- ኢትዮጵያውያን**

- ✓ የፀና ፓስፖርት ቅጂ
- ✓ የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅ መታወቂያ ካርድ ቅጂ
- ✓ ያገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
- ✓ ያላገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን
- ✓ ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
- ✓ ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትደር ጓደኛ ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤት ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
- ✓ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ በዩሮ ፣ በፓውንድ) የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመወሰድ ዝግጁ የሚሆን፣
- ✓ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በግል በባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ፣

**በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች**

- ✓ በግል የሚመዘጉ የዳያስፖራ አባላት የሚፈልጉትን ክልል/ከተማ አስተዳደር በመምረጥ የሚፈልጉትን የቤት ዓይነት ይመርጣሉ፣
- ✓ ቤቱን ለመገንባት ከሚያስፈለገው ወጪ ደረጃ የሚጠበቅባቸውን 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት ከሚኖሩበት ሀገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ሂሳብ በመክፈት ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ቤት በመላክ ወደ ተከፈተው አካውንት ያስተላለፉበትን ደረሰኝ ቅጂ ተሞልቶ ከተፈረመው የመመዝገቢያ ቅጽ ጋር በማያያዝ ለሚሲዮኑ ያቀርባሉ፡፡
- ✓ በግል የተመዘገቡ የዳያስፖራ አባላት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት ዝቅተኛውን ቁጥር ሲያሟሉ ሚሲዮኑ በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ መረጃውን ወደ ዋናው መ/ቤት የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡

- ✓ የግል ተመዝጋቢዎችን በተመዘገቡበት ሚሲዮን በሚኖሩበት አገር በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት በማህበር ዝቅተኛው ቁጥር የማይሞሉ ከሆነ ከሚሲዮኑ መረጃቸው በሽኚ ደብዳቤ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡
- ✓ በግል የመጡ መረጃዎችን ወደ መረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር በዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አማካኝነት ይላካል፡፡
- ✓ ክልሉ/ከተማ አስተዳደር በተመሳሳይ መልኩ ከሌላ ሚሲዮን ዝቅተኛውን የማህበር አባላት ቁጥር ሳይሞላ ከተላኩ ጋር በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ መረጃውን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለተወካየቻቸው ያሳውቃል፡፡

<u>በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው የሚመዘገቡት የዳያስፖራ አባላት</u>

- ✓ በመጀመሪያ መደራጀት የሚፈልጉበትን ክልል/ከተማ አስተዳደር ይመርጣሉ፣
- ✓ በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት የአባላቱን ቁጥር ይወስናሉ፡፡
- ✓ የመስራች ስብሰባ ለመሥራት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበር መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማህበራቸውን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተው ያፀድቃሉ፣ ማህበሩን ይመሠረታሉ፡፡
- ✓ በምስረታው ስብሰባው የሥራ አመራር ም/ቤት  የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የቴክኒክና የማህበራዊ ኮሚቴ እና እንደ አስስፈላጊነቱ ሌሎችንም ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፡፡ የአመራር አባላትም ምርጫ ያደርጋሉ፡፡
- ✓ ሁሉም የማህበሩ አባላት የመራሪች ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና የመስራች አባላት ዝርዝር ቅጽ ላይ ፊርማቸውን ያኖራሩ፣
- ✓ ማህበሩ በህጋዊ መንገድ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር መመዝገብ የሚችለው ሁሉም የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ በዩሮና በፓውንድ) በምዝገባ ወቅት መክፈል ሲችሉ እና መሬት ተዘጋጅ ማህባሩ ሲረከብ የቀሪውን 50 በመቶ ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ ሲሆኑ ብቻ ይሆናል፡፡
- ✓ ማህበሩ የእያንዳንዳን አባል የተሟላ ሰነድና ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኝ በማያያዝ በሚሲዮኑ ወይም ሚሲዮኑ በሚያመቻቸው የምዝገባ ቦታ ወይም በኢትዮጵያ ህዳሴ ም/ቤቶች ዘንድ በአካል ተገኝተው ምዝገባ ያካሂዳሉ፡፡
- ✓ የኢትዮጵያ ህዳሴ ም/ቤቶች መስፈርቱን አሟልቶ የተደራጁ ማህበራትን ሰነድ ከተቻለ በአካል ካልሆነም በተመዘገበ ፖስታ ለሚሲዮኑ በአድራሻ ይልካሉ፡፡ ስለመድረሱም መተማመኛ ከሚሲዮኑ ይረከባል፡፡ ለማህበሩ የመተማመኛውን ኮፖ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ሚሲዮኑ የተደራጁ ማህበራት ሙሉ መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በፓውች ይልካል፡፡ ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉም የማህበራቱ ሰነድ ስለመድረሱ ለሚሲዮኑ ያሳውቃል፡፡
- ✓ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የማህበራቱን ሙሉ መረጃ ከሽኚ ደብዳቤ ጋር ለመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር እንዲያደርሱ ለማህበራቱ ተወካዮች ስለመቀበላቸው አስፈርሞ ያስረክባል፡፡
- ✓ ክልሉ/ከተማ አስተዳድሩ ለማህበራቱ እውቅና መስጠቱን፣ መሬትና የግንባታ ፈቃድ መዘጋጀቱን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራልና ለማህበራቱ ተወካዮች ያሳውቃል፡፡
- ✓ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ለመኖሪያ ህብረት ሥራ ማህበሩ እውቅና መስጠቱን እንዲሁም መገኘቱን፣ ለማህበሩ መሬትና የግንባታ ፈቃድ መዘጋጀቱን ለሚሲዮኑ ይገልጻል፡፡
- ✓ ሚሲዮኑ ይህንኑ ለማህበራቱ ያሳውቃል፡፡
- ✓ ማህበሩ ሁሉም አባላት ቀሪውን 50 በመቶ ወደ ማህበራቱ ዝግ አካውንት ማስተላለፋቸውን በማረጋገጥ መረጃውን ለሚሲዮኖች ያሳውቃል፡፡
- ✓ ሚሲዮኑ ቀሪውን 50% ክፍያ ፈፅመው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያስተላልፋል፡፡
- ✓ የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ጄኔራል ቀሪውን 50% ክፍያ ፈፅመው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ለማህበሩ ተወካያችና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያሳውቃል፡፡

- ✓ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማህበሩ አካላት ለቤቱ ግንባታ የሚያስፈልገውን 100% በወጪ በውጭ መንዛሪ ማስገባታቸውን፣ ቀጥሎም በብር ወደ ማህበሩ አካውንት መተላለፉን በማረጋገጥ ለክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የማህበራት አደራጅ አካልና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳ/ጄኔራል ያረጋግጣል፡፡
- ✓ የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አደራጅ አካል ማህበራቱ የግንባታውን 100% ከፍለው ማጠናቀቃቸውን ከኢትያጵያ ንግድ ባንክ ማረጋገጫ ሲደርሰው ለማህበራቱ መሬትና የግንታታ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይለካል፣ ለማህበራቱ ተወካዮች በግልባጭ ያሳውቃል፡፡

| የሚገነቡ ቤቶች ዓይነት ስፋትና ዋጋ ያቀረቡ ክልሎች። | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረር | | | | |
| 2 | ትግራይ | | | | |
| 3 | ድሬዳዋ | | | | |
| 4 | አማራ | | | | |
| 5 | ሶማሌ | | | | |
| 6 | ጋምቤላ | | | | |
| 7 | ደቡብ | | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | | | | |

| ተ.ቁ | ክልል | የአፓርትመንት ዓይነት | መኝታቤት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረር | G+4 እና በላይ | ባለ 2 | 74 ካሜ | 424.390 |
| | | | ባለ 3 | 100 ካሜ | 573.500 |
| | | | ባለ 4 | 136 ካሜ | 779.960 |
| | | G+2 አማራጭ | ባለ 3 | 114 ካሜ | 693.120 |
| | | | ባለ 4 | 150 ካሜ | 912.00 |
| | ታውን ሀውስ የክልሉን | G+2 | ባለ 6 | 181.18 ካሜ | 1.101.574 |
| | ኪነ ሕንጻ ጥበብ ያማከለ | G+1 | ባለ 4 | 129.63 ካሜ | 788.150 |
| | | G+1 | ባለ 7 | 247.55 ካሜ | 1.505.104 |
| 2 | ትግራይ | G+2 እና በላይ | ባለ 2 | 74 ካሜ | 424.390 |
| | | | ባለ 3 | 100 ካሜ | 573.500 |
| | | | ባለ 4 | 136 ካሜ | 779.960 |
| 3 | ድሬዳዋ | ታውን ሀውስ | ባለ 2 | 128 ካሜ | 582.400 |
| | | | ባለ 3 | 160 ካሜ | 728.000 |
| | | | ባለ 4 | 200 ካሜ | 910.000 |
| | | G+1 እና G+2 ታውን | ባለ 2 | 160 ካሜ | ዋጋ አልተቀመጠም |
| | | ሃውስ ቤቶች | ባለ 3 | 200 ካሜ | ዋጋ አልተቀመጠም |
| | | | ባለ 4 | 250 ካሜ | ዋጋ አልተቀመጠም |
| 4 | አማራ | G+4 እና በላይ | ባለ 2 | 74 ካሜ | 424.390 |
| | | | ባለ 3 | 100 ካሜ | 573.500 |
| | | | ባለ 4 | 136 ካሜ | 779.960 |
| | | ታውን ሀውስ G+2 | ባለ 3 | 114 ካሜ | 693.120 |
| | | | ባለ 4 | 150 ካሜ | 912.00 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ሶማሌ | G+4 እና በላይ | ባለ 2 | 74 ካሜ | 424.390 |
| | | | ባለ 3 | 100 ካሜ | 573.500 |
| | | | ባለ 4 | 136 ካሜ | 779.960 |
| | | ታውን ሀውስ G+2 | ባለ 3 | 114 ካሜ | 693.120 |
| | | | ባለ 4 | 150 ካሜ | 912.00 |
| 6 | ጋምቤላ | G+4 እና በላይ | ባለ 2 | 74 ካሜ | 424.390 |
| | | | ባለ 3 | 114 ካሜ | 693.120 |
| | | | ባለ 4 | 150 ካሜ | 912.000 |
| | በዞን ዋና ከተሞች | ታውን ሀውስ G+2 | ባለ 3 | 114 ካሜ | 693.120 |
| | | | ባለ 4 | 150 ካሜ | 912.00 |
| 7 | ደቡብ | መሪ ከተማ G+4 አፓርትመንት/ሀዋሳ/ | ባለ 2 | 80ካሜ | 770.720.96 |
| | | | ባለ 3 | 95 ካሜ | 824.911.15 |
| | | | ባለ 4 | 110ካሜ | 876.049.35 |
| | አርባ ምንጭ፣ወላይታ ሶዶ፣ሆሳእና | ከፍተኛ የከተማ አስተ ዳደር ከተሞች G+3 አፓርትመንት | ባለ 2 | 85ካሜ | 840,208.61 |
| | | | ባለ 3 | 100 ካሜ | 926,571.12 |
| | | | ባለ 4 | 115 ካሜ | 959,128.58 |
| | ወልቂጤ፣ቡታጅራ፣ ሚዛን አማን፣ቴፒ፣ ይርጋለም | መካከለኛ የከተማ አስ ተዳደርከተሞች G+2 ታውን ሃውስ | ባለ 2 | 90ካሜ | 840,076.79 |
| | | | ባለ 3 | 105 ካሜ | 912,422.86 |
| | | | ባለ 4 | 120 ካሜ | 956,890.70 |
| | ወራቤ፣ሀላባ፣ይርጋ ጨፌ፣አለታ ወንዶ፣ በቦዲቲ፣አረካ፣ዱራሜ ቦንጋ፣ሳውላ፣ጂንካና ተርጫ | ተታዳጊ የከተማ አስ ተዳደር ማዘጋጃ ቤትና የታዳጊ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች G+ ታውን ሃውስ ቤቶች | ባለ 2 | 80ካሜ | 204,544.70 |
| | | | ባለ 3 | 90 ካሜ | 242,378.78 |
| | | | ባለ 4 | 100ካሜ | 278,736.00 |
| 8 | ኦሮሚያ | አፓርታማ G+1 እና G+2 | ባለ 2 | 80 ካሜ | 400.000 |
| | | | ባለ 3 | 100 ካሜ | 550.000 |
| | | ታውን ሀውስ የከተማ ቤት | ባለ 4 | 110 ካሜ | 700.000 |
| | | | | 80 ካሜ | 800000 |

ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርቶች በማሟላት እ.ኤ.አ. 29-04-2015 ጀምሮ መመዝገብ እንደሚቻል እንገልፃለን።

የኢፌዲሪ ቆንስላ ጄኔራል ፅህፈት ቤት ፍራንክፈርት